የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ–መስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 1
ADDIS ABABA - 12th October, 1998

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፩/፲፱፻፺፩ ዓ·ም
የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................ ገጽ ፰፻፵፰

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 41/1998
Leather and Leather Products Technology Institute Establishment Council of Ministers Regulations ............................................ Page 848

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፩/፲፱፻፺፩
### የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፩/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው ።

፫· መቋቋም

፩· የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት /ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩቱ" ተብሎ የሚጠራ/የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ።

### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 41/1998*
### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF LEATHER AND LEATHER PRODUCTS TECHNOLOGY INSTITUTE*

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Leather and Leather Products Technology Institute Establishment Council of Ministers Regulations No. 41/998."

2. *Definitions*

In these Regulations,

"Ministry" or "Minister" means the Ministry or the Minister of Trade and Industry, respectively.

3. *Establishment*

1) There is hereby established the Leather and Leather Products Technology Institute (hereinafter "the Institute") as an autonomous federal government institution having its own legal personality.

፪· የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

፬· <u>የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ይሆናል ፣ እንደአስፈላጊነቱም በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ማቋቋም ይችላል ።

፭· <u>የኢንስቲትዩቱ ዓላማ</u>

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ ስለተለያዩ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች አሠራር ፣ ከቆዳና ከቆዳ ውጤቶች ፋብሪካ ጋር ስለተገናኙ ጥሬ ዕቃዎች ፣ ኬሚካልና መካኒካል አሠራሮች እና ስለጥራት ቁጥጥር ዘዴዎች የተግባርና የፅንሰ–ሀሣብ ሥልጠናዎችን በመስጠት እንዲሁም በመስኩ የምርምርና የምክር አገልግሎት ሥራዎች በማካሄድ ለዘርፉ የሠለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት ይሆናል።

፮· <u>የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ለሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሕግ ተለይተው የተሰጡት ሥልጣንና ተግባሮች እንደተጠበቁ ሆነው ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

፩· በተለያዩ ደረጃዎች የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ቴክኖሎጂ ሥልጠናዎችን በመስጠት በዘርፉ የሙያተኞችን ብዛት ማሳደግ ፣

፪· የቆዳና የቆዳ ውጤቶችን ጥራትና ብዛት ለማሳደግ የሚያስችሉ የምርምርና ልማት ተግባራትን ማከናወን ፣

፫· የቆዳና የቆዳ ውጤቶችን የጥራት ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችሉ የምክር አገልግሎቶችን መስጠት ፣

፬· የዘርፉን ልማት ለማሳደግ የሚያስችሉ የመረጃ አገልግሎቶችን መስጠት ፣

፭· ለሚያሰለጥናቸው ባለሙያዎች የምስክር ወረቀት መስጠት ፣

፮· ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ክፍያ ማስከፈል ፣

፯· የንብረት ባለቤት መሆን ፣ ውል መዋዋል ፣ በራሱ ስም መክሰስ እና መከሰስ ፣

፰· ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን።

፯· <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ፣

፩· የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርዱ" እየተባለ የሚጠራ) ፣

፪· በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም አንድ ዲሬክተር ፣

፫· አካዳሚክ ካውንስል ፣ እና

፬· አስፈላጊ ሠራተኞች ፣

ይኖሩታል።

፰· <u>የቦርዱ አባላት</u>

፩· ቦርዱ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ በመንግሥት የሚሰየሙ ሰባት አባላት ይኖሩታል ፣

፪· የቦርዱ ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል በመንግሥት ይመደባል።

2) The Institute shall be accountable to the Ministry.

4. *Head Office*

The Institute shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices in other places, as may be necessary.

5. *Objectives*

The objectives of the Institute shall be to produce trained manpower for the sector by providing theoretical and practical trainings, and conducting research and consultancy activities in all aspects of leather and leather products manufacture, raw materials, chemical processes, mechanical operations and quality control methods.

6. *Powers and Duties*

Without prejudice to specific powers and duties given by law to other government institutions, the Institute shall have the following powers and duties:-

1) to increase the number of professionals of the sector by providing trainings at various levels in leather and leather products technology;
2) to undertake applied research and development activities which can improve the quality and quantity of leather and leather products;
3) to upgrade the quality standards of leather and leather products by providing consultancy services;
4) to provide information services which facilitate the growth of the sector;
5) to confer academic certificates and diplomas to trainees;
6) to charge fees for services it renders;
7) to own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;
8) to engage in other activities necessary to accomplish its objectives.

7. *Organization of the Institute*

The Institute shall have:-

1) a Board of Management (hereinafter the ''Board'');
2) a Director to be appointed by the government upon the recommendation of the Minister;
3) an Academic council; and
4) the necessary staff.

8. *Members of the Board*

1) The Board shall constitute seven members to be designated by the Government from private sector and government institutions.
2) The Chairperson shall be assigned by the Government from among the members of the Board.

፱· <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩· የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች በበላይነት የመቆጣጠር ፣ የመከታተል እና ኢንስቲትዩቱ በዓላማው መሠረት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረጉን የማረጋገጥ ፤

፪· የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሠረታዊ መርሆዎች በመከተል የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን መመሪያዎች የማፅደቅ ፣ የሠራተኞችን የደመወዝ ስኬልና ሌሎች የማነቃቂያ ክፍያዎችን የመወሰን ፣ ተግባራዊነታቸውንም የመከታተል ፤

፫· ለዲሬክተሩ በቀጥታ ተጠሪ የሆኑ ኃላፊዎችን ቅጥር ፣ ምደባና ስንብት የማፅደቅ ፤

፬· ኢንስቲትዩቱ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚያስከፍለውን የክፍያ ተመኖች የመወሰን ፤

፭· ኢንስቲትዩቱ ከአገር ውስጥ ወይም ከውጭ አገር ተቋማት ጋር የሚያደርጋቸውን ስምምነቶች የማፅደቅ ፤

፮· የኢንስቲትዩቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ለሚኒስቴሩ የማቅረብ ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን የመቆጣጠር ፤

፯· ይህንን ደንብ መሠረት በማድረግ የሚዘጋጁ የኢንስቲትዩቱን የውስጥ ደንቦች የማፅደቅ ፣ ተግባራዊነታቸውንም የመከታተል ፤

፰· በኢንስቲትዩቱ ዲሬክተር በሚቀርቡ ሌሎች የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ የመምከር ፣ የመወሰን ፤

፱· ለኢንስቲትዩቱ ዲሬክተር አጠቃላይ የሥራ መመሪያ የመስጠት ፤

፲· የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ገምግሞ ከአስተያየት ጋር ለሚኒስቴሩ የማቅረብ።

፲· <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

፩· ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል ፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

፪· በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላት ከተገኙ ምልዐተ—ጉባዔ ይሆናል።

፫· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ ውሳኔ የሚሰጠው በድምፅ ብልጫ ይሆናል ፤ ሆኖም ድምፅ እኩል ለእኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

፬· የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ—ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፲፩· <u>የዲሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩· ዲሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል ፣ ያስተዳድራል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ዲሬክተሩ፡

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል ፤

ለ) የኢንስቲትዩቱን የሠራተኞች አስተዳደር መመሪያ፣ የደመወዝ ስኬልና ሌሎች የማነቃቂያ ክፍያዎች አጥንቶ ለቦርዱ ያቀርባል ፣ ሲፈቀደም ተግባራዊ ያደርጋል ፤

*9. Powers and Duties of the Board*

The Board shall have the following powers and duties:

1) to supervise and follow-up the activities of the Institute and ensure that it functions in accordance with its objectives;
2) to approve directives, based on the general principles of federal civil service laws, for the employment and administration of the staff of the Institute; to determine salary scales and other incentives and follow up the implementation of same;
3) to approve the employment, assignment and dismissal of officials directly accountable to the Director;
4) to determine fees to be charged by the Institute for the services it renders;
5) to endorse agreements to be concluded by the Institute with local or foreign institutions;
6) to submit the work program and budget of the Institute to the Ministry and, upon approval, supervise the implementation of same;
7) to approve the internal regulations of the Institute to be prepared pursuant to these Regulations, and follow-up the implementation of same;
8) to deliberate and decide on other policy issues proposed by the Director;
9) to give general directives to the Director;
10) to evaluate the performance report of the Institute, quarterly, and submit same to the Ministry together with its comments.

*10. Meetings of the Board*

1) The Board shall have a regular meeting every month; it may, however, convene extraordinary meetings as deemed necessary.
2) There shall be a quorum where more than half of the members of the Board are present.
3) without prejudice to the provisions of sub-Article (2) of this Article, the Board shall decide by a majority vote. In case of a tie the Chairperson shall have a casting vote.
4) Subject to the provisions of this Article, the Board may issue its own rules of procedure.

*11. Powers and Duties of the Director*

1) The director shall be the chief executive officer of the Institute and, as such shall, subject to the general directives of the Board, direct and administer the activities of the Institute.
2) Without limiting the generality of sub-Article (1) of this Article, the Director shall:
   (a) exercise the powers and duties of the Institute specified in Article 6 of these Regulations;
   (b) study and submit to the Board the administrative manual, salary scale and other incentives of the Institute and implement same upon approval;

ሐ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል ፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል ፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል ፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈፃፀምና የሒሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል።

፫· ዲሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

፲፪· ስለአካዳሚክ ካውንስል አባላት

የኢንስቲትዩቱ አካዳሚክ ካውንስል የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡

፩· የኢንስቲትዩቱ ዳሬክተር .......................... ሰብሳቢ
፪· ሬጅስትራር .......................................... አባል
፫· የተማሪዎች ተወካይ .................................. "
፬· የመምህራን ተወካይ .................................. "
፭· ከኢንስቲትዩቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች በቦርዱ የሚሰየሙ ተወካዮች .............................. "

፲፫· የአካዳሚክ ካውንስሉ ሥልጣንና ተግባር

የአካዳሚክ ካውንስሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተገባሮች ይኖሩታል፡

፩· የኢንስቲትዩቱን ልዩ ልዩ የትምህርት ፕሮግራምና ካሌንደር መርምሮ ለቦርዱ የማቅረብ ፤
፪· ዲፕሎማ ፣ ሠርቲፊኬትና ልዩ ሽልማት የሚሰጥበትን ሁኔታ እያጠና ለቦርዱ የማቅረብ ፤
፫· የተማሪዎችና ሠልጣኞች አቀባበልን ፣ የትምህርት ደረጃ አወሳሰንን ፣ ምዘናን፣ የዲሲፕሊንና የምረቃ ጉዳዮችን የሚመለከቱ መመዘኛ መስፈርቶችን አዘጋጅቶ ለቦርዱ የማቅረብ ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ የማድረግ ፣ በነዚህ ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችንና ቅሬታዎችን መርምሮ ውሳኔ የመስጠት ፤
፬· አጠቃላይ የፈተና አሰጣጥ ዘዴና ሁኔታን የመወሰን ፤
፭· ስለአካዳሚክ እድገቶች ጉዳይ አጥንቶ ለቦርዱ የማቅረብ፡
፮· ወደሚቀጥለው የትምህርት እርከን የሚሸጋገሩ ተማሪዎችን ዝርዝር መርምሮ የመወሰን ፤
፯· የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ የመወሰን ፤
፰· በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች የማከናወን ።

፲፬· በጀት

የኢንስቲትዩቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል ፤

፩· በፌዴራል መንግሥት ከሚመደብለት የገንዘብ ድጎማ ፤
፪· ከሚሰበሰበው የአገልግሎት ክፍያ፣ እና
፫· ከዕርዳታ፣ ከስጦታ እና ከማናቸውም ሌሎች ምንጮች ከሚያገኘው ገቢ ።

፲፭· የሒሳብ መዛግብት

፩· ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብት ይይዛል።

(c) prepare and ubmit to the Board the work program, and budget of the Institute and implement same upon approval;
(d) effect payment in accordance with the approved budget and work program of the Institute;
(e) represent the Institute in its dealings with third parties;
(f) submit to the Board the performance and financial reports of the Institute.

3) The Director may delegate part of his powers and duties to officers and other employees of the Institute to the extent necessary for the effective performance of the activities of the Institute.

*12. Members of Academic council*

The Academic Council of the Institute shall consist of the following members:

1) the director of the Institute ...................... Chairman
2) the registrar of the Institute ...................... member
3) the Student's representative ........................ ''
4) the Teacher's representative ........................ ''
5) representatives from the various Departments of the Institute to be designated by the Board ''

*13. Powers and Duties of the Academic Council*

The Academic Council shall have the following powers and duties:-

1) to examine and submit to the board the academic program and calendar of the Institute;
2) to undertake study on the conferring of diplomas, certificates and special awards and submit it to the board;
3) to prepare and submit to the board, criteria for admission of students and trainees, determination of academic standards, evaluation, disciplinary and graduation matters, and implement same upon approval; examine and decide on grievances and complaints on these matters;
4) to determine methods and conditions of examination;
5) to study and summit to the Board promotions in academic rank;
6) to examine and decide on the list of students to be promoted to the next academic level;
7) to determine its own rules of procedure;
8) to perform such other duties as may be given to it by the Board.

*14. Budget*

The budget of the Institute shall be drawn from the following sources:

1) financial subsidy allocated by the Federal Government;
2) fees collected from its services; and
3) grants, donations and any other sources of income.

*15) Books of Account*

1) The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

፪. የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

፲፮. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ መስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

2) The books of accounts and financial documents of the Institute shall be annually audited by the Auditor General or by an external auditor assigned by him.

16. *Effective Date*

These Regulations shall come into force on the date of their publications in the Federal Negarit Gazetta.

Done at Addis Ababa, this 12th day of October , 1998.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA